# Housing Counseling Services, Inc.

## የመኖሪያ ቤት የምክር አገልግሎቶች (ሀውዚንግ ካውንስሊንግ ሰርቪስስ) (ኤች.ሲ.ኤስ.)
## ዲ.ሲ. የአከራይ እርዳታ መርጃ ሀብቶች (ዲ.ሲ. ቴናንት አሲስታንስ ሪሶርስስ)

የመኖሪያ ቤት በተመለከተ አስቸኳይ ነገር ገጥሞዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎት አያውቁም? የመኖሪያ ቤት የምክር አገልግሎቶች (ሀውዚንግ ካውንስሊንግ ሰርቪስስ) (ኤች.ሲ.ኤስ.) እርስዎን መርዳት የሚችሉ መርጃ ሀብቶች አለው! ምንም እንኳን ለኪራይ እዳ ሊውሉ የሚችሉ የመንግስት መርጃ ሀብቶች ውሱን ቢሆኑም፣ እነዚህ መርጃ ሀብቶች ከቤትዎ በግድ እንዳይወጡ በማድረግ እና ከቤት አልባነት በመከላከል የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ እና እንዲረጋጉ ሊረዳዎ ይችላል።

- አስቸኳይ የኪራይ እርዳታ ፕሮግራም (ኢመርጀንሲ ሬንታል አሲስታንስ ፕሮግራም) (ኢራፕ)፡ በበጀት ገደቦች ምክኒያት፣ የኢራፕ ማመልከቻ መግቢያ ሲስተም (ፖርታል) በማርች 10፣ 2023 ተዘግቶ ነበር። ከመዘጋቱ በፊት የተላኩ የኢራፕ ማመልከቻዎች በሂደት ላይ ናቸው። ያቀረብዎት የኢራፕ ማመልከቻ ያለው ደረጃ ለማወቅ እና መግቢያ ሲስተሙ (ፖርታል) አዳዲስ የኢራፕ ማመልከቻዎች ለመቀበል መቼ እንደሚከፈት በተመለከተ መረጃ ለማግኘት በኦንላይን በhttps://erap.dhs.dc.gov/ ይጎብኙ ወይም በ202-507-6666 ይደውሉ።

- ቤት አልባ የመሆን አደጋ ላጋጠማቸው ተከራዮች የመንግስት መርጃ ሀብቶች፡ ቤት አልባነት ወይም የመኖሪያ ቤት አለመረጋጋት ያጋጠማቸው አካለ መጠን ያልደረሱ ህጻናት ያላቸው የዲሲ ነዋሪዎች፣ ቨርጂኒያ ዊልያምስ ሪሶርስ ሰንተርን የተባለው መርጃ ማርከልን በ 202-526-0017 ማግኘት ይችላሉ። ያላገቡ ግለሰቦች (ሲንግል ኢንዲቪጁዋልስ) ፕራጀክት ኮነክት የተባለውን ድርጅት በ Project.Reconnect@dc.gov መድረስ ይችላሉ።

- የቀድሞ ወታደሮች (ቬተራንስ)፡ ቤት አልባ ለሆኑ ወይም ቤት አልባ የመሆን አደጋ ላይ ለሆኑ የቀድሞ ወታደሮች የኤች.ሲ.ኤስ. ለየቀድሞ ወታደሮች ቤተሰቦች የድጋፍ አገልግሎቶች (ኤች.ሲ.ኤስ. ሳፖርቲፍ ሰርቪስስ ፎር ቬተራን ፌሚሊስ) (ኤስ.ኤስ.ቪ.ኤፍ.) ፕሮግራም የጉዳይ አስተዳደር (ኬዝ ማኔጅመንት) እና ለኪራይ፣ ዩቲሊቲዎች፣ እና ሌሎች መሰረታዊ አስፈላጊ ነገሮች የፋይናንስ እርዳታ ያቀርባል። በ202-667-7366 ይደውሉ ወይም ወደ ssvfprogram@housingetc.org ኢመይል ይላኩ።

- ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ያላቸው ሰዎች (ፒ.ኤል.ዳብሊው.ኤች.ኤ.)፡ የኤች.ሲ.ኤስ. ኤም.ኤች.ኤ.ፒ. ፕሮግራም ብቁ ለሆኑ ኤች.አይ.ቪ. ላላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች የጉዳይ አስተዳደር (ኬዝ ማኔጅመንት) እና ለኪራይ፣ ሞርጌጅ፣ ዩቲሊቲዎች፣ ምግብ፣ ቤት መቀየሪያ ወጪዎች፣ እና ሌሎች መሰረታዊ አስፈላጊ ነገሮች የሚውል የፋይናንስ እርዳታ ያቀርባል። ወደ 202-900-9471 ይደውሉ ወይም ወደ email mhap@housingetc.org ኢመይል ይላኩ።

- የህግ መርጃ ሀብቶች (ሊጋል ሪሶርስስ)፡ የአከራይና ተከራይ የህግ እርዳታ መርበብ (ላንድሎርድ ቴናንት ሊጋል አሲስታንስ ኔትዎርክ) (ኤል.ቲ.ኤል.ኤ.ኤን.) ብቁ ለሆኑ የዲ.ሲ. ነዋሪዎች ነጻ የህግ ድጋፍ ያቀርባል። ኤል.ቲ.ኤል.ኤ.ኤን.ን በቴሌፎን ቁጥር 202-780-2575 ይደውሉ ወይም በኦንላይን ወደ https://www.dcbar.org/pro-bono/free-legal-help/help-for-individuals/housing-legal-assistance በመሄድ ይጎብኙ። ለሌላ የህግ እርዳታ የዲ.ሲ. የተከራይ ተሟጋች ጽህፈት ቤት (ዲ.ሲ.ስ ኦፊስ ኦፍ ዚ ቴናንት አድቮኬት) በ (202) 719-6560 ያግኙ። በፍርድ ቤት ከቤት እንዲወጡ በሚል ክስ (ኢቪክሽን) የተከሰሱ ከሆነ፡ የህግ እገዛ እንዲደረግልዎ ይጠይቁ፣ በሁሉም ችሎቶች ይሳተፉ፣ እና መርጥ አያስፈልግም። ፍርድ ቤት ትእዛዝ ካስተላለፈ የዩ.ኤስ. ማርሻሎች ብቻ ናቸው የከቤት ማስወጣት ትእዛዝ ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉት!

- የተከራይ መብቶች፡ እየኖሩበት ያለ ህንጻ ሲሸጥ፣ መጥፎ የመኖሪያ ቤት ሁኔታ ሲኖር ሲወያዩ፣ እና የተከራይ ማህበር ሲያደራጁ የተከራይ መብቶች በተመለከተ ለመወያየት የኤች.ሲ.ኤስ. የተከራይ አገልግሎቶች (ቴናንት ሰርቪስስ) ቡድን በ (202) 900-9464 ይደውሉ ወይም ወደ tenants@housingetc.org ኢመይል ይላኩ።

- ፍትሀዊ የመኖሪያ ቤት መብቶች (ፈይር ሀውዚንግ ራይትስ)፡ ፍትሀዊ የመኖሪያ ቤት መብቶችዎ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ቢፈልጉ እና የመኖሪያ ቤት አድልዎ ቅሬታዎች ፋይል ለማድረግ እገዛ ቢፈልጉ የኤች.ሲ.ኤስ. ፍትሀዊ የመኖሪያ ቤት ቡድንን በ 202-681-8386 ወይም በ ronaldclarkson@housingetc.org ያግኙ።

- የመኖሪያ ቤት የምክርና የበጀት እገዛ፡ የኤች.ሲ.ኤስ. ራይዝ ፕሮግራም ተከራዮች ኪራይ መክፈልን ቅድሚያ የሚሰጥ ባጀት ለመስራት የሚረዳ፣ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ከመኖሪያ ቤት የመውጣት አደጋ ለመቀነስ ያሉትን አማራጮች በተመለከተ ለማወቅ የሚረዳ፣ እና ከአከራይዎ ጋር የአከፋፈል እቅድ በተመለከተ ለመደራደር የመኖሪያ ቤት ምክር (ሀውዚንግ ካውንስሊንግ) ይሰጣል። በ rise@housingetc.org ያግኙን።

- የተረጋጋ መኖሪያ ቤት ያሳኩ (አቺቭ ስቴብል ሀውዚንግ)፡ የተረጋጋ መኖሪያ ቤት (ስቴብል ሀውዚንግ) ማሳካትን በተመለከተ ለመማር የኤች.ሲ.ኤስ. የዌቢናር ስብሰባዎች (በኢንተርኔት የሚደረጉ ስብሰባዎች) ይቀላቀሉ፡
  ለዌቢናር ስብሰባዎቹ በ www.housingetc.org በመጎብኘት ወይም ወደ 202-667-7606 በመደወል ይመዝገቡ።
  - የተከራይ መብቶችና መርጃ ሀብቶች የዌቢናር ስብሰባ (ቴናንት ራይትስ ኤንድ ሪሶርስስ ዌቢናር) - ራስዎን እንዴ መከላከል እንደሚችሉና የመኖሪያ ቤትዎን እንዴት እንደሚያረጋጉ ይማሩ።
  - የኪራይ ቤቶች ፍለጋ የዌቢናር ስብሰባ (ሬንታል ሀውዚንግ ሰርች ዌቢናር) - መኖሪያ ቤት የማግኘት መንገዶች በተመለከተ ይማሩ።
  - የገንዘብ ጉዳዮች የዌቢናር ስብሰባ (ማኒ ማተርስ ዌቢናር) - ባጀት ማድረግ በተመለከተ ይማሩ።
  - የአካታች ማካለል የዌቢናር ስብሰባ (ኢንክሉዥናሪ ዞኒንግ ዌቢናር) - ተመጣጣኝ ክፍያ ለሚከፈልበት የአይ.ዚ. ኪራዮች እንዴት ብቁ መሆን እንደሚችሉ ይማሩ።

ስለነዚህ እና ስለ ሌሎች የመኖሪያ ቤት የምክር አገልግሎቶች ፕሮግራሞች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን በድረገጽ www.housingetc.org ያግኙ ወይም ወደ info@housingetc.org ኢመይል በመላክ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

(የተሻሻለበት ቀን፡ ኤፕሪል 2023/Updated April 2023)